# ደንብ ሞንትጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS)

ተዛማጅ ሠነዶች፦ CNA, CNBRA, CND, EGB-RA, EGCRA, IPD-RA, IGT-RA, JFA-RA, KBA-RA

ኃላፊነት ያለው ቢሮ፦ የግንኙነት ክፍል/ዲፓርትመንት
የድህረ ገፅ አገልግሎቶች

የትምህርት አላማዎች እና የ **MCPS Web** / ድረ-ገፅ አስተዳደር

## I. ዓላማ

የዚህ ደንብ አላማ ለሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) Web ድረ-ገፅ ቅርፅ እና ይዘት ንድፈ-ሀሳብ/መዋቅር ማቅረብ ነው። ይሄ ንድፈ-ሀሳብ ድህረ-ገፁ ለ MCPS ትምህርታዊ አላማ እንዲውል በ MCPS Web / ድረ-ገፅ ላይ ለሚታተሙ መረጃዎች ተጠያቂነትን ይሰጣል፤ በአለም-አቀፋዊ ግንኙነት ምህዳር ውስጥ የ MCPS ሰራተኞች እና ተማሪዎችን ሚስጥራዊነት ለመጠበቅ ምክንያታዊ ቁጥጥሮችን ይዘረጋል፤ እና የ MCPS ድረ-ገፅ ምርጥ ተሞክሮዎችን ማካተቱን እና ከፍተኛውን የትምህርት እና የጥራት ደረጃዎች መጠበቁን ያረጋግጣል።

## II. የቀድሞ መነሻ

ለወላጆች፣ ተማሪዎች፣ እና ለመላው ማህበረሰብ ጠቃሚ መረጃን እና ቴክኒካዊ ድጋፍ ለትምህርታዊ፣ አስተዳደራዊ፣ እና የስራ አፈፃፀም መገለጫዎችን ስለ ት/ቤቱ ስርዓት ለማቅረብ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ትክክለኛ የዲስትሪክት፣ የት/ቤት እና የቢሮ ድህረ-ገፆችን ስራ በአግባቡ ያስቀጥላል። የ MCPS Web / ድረ-ገፅ ይፋዊ/የህዝብ ያልሆነ መድረክ ነው። MCPS መብት አለው፣ እና መብቱን ለመጠቀም መርጧል፣ ይሄም በ MCPS ድረ-ገፅ በኩል የሚለቀቁ እና ተደራሽ የሚሆኑ ግብዓቶች ላይ ምክንያታዊ እገዳዎችን ማስቀመጥ ነው።

## III. ፍቺ/ትርጓሜ(ዎች)

A. የማውጫ መረጃ መያዣ ዝርዝር / *Directory Information Withhold List* ማለት ት/ቤቶች በግል መረጃዎችን ለማግኘት ግልፅ ማድረግ ላይ እገዳ የሚያደርግባቸው የተማሪዎች ዝርዝር ነው። የማውጫ መረጃ መለቀቅን ለማገድ፣ ወላጅ ወይም ብቁ የሆነ ተማሪ መያዝ ስላለበት የተለየ መረጃ ለት/ቤት ዳይሬክተር ማሳወቅ አለበት፣ ሁሉም በደንብ JOA-RA፦ የተማሪ

መዝገቦች ላይ በተቀመጠው መሰረት ነው የሚሆነው።

B. ትምህርታዊ አላማዎች ማለት ቀጥተኛ በሆነ መንገድ የ MCPS ትምህርታዊ፣ የትምህርት አሰጣጥ፣ አስተዳደራዊ፣ የቢዝነስ እና የድጋፍ አገልግሎቶች ተልዕኮዎችን የሚያስተዋውቁ፣ እና ተጠቃሚው ሀላፊነት የሚወስድባቸውን ማንኛውም ትምህርታዊ፣ የተሰጥ ስራ/ፕሮጀክት፣ ስራ፣ የስራ ምደባ፣ ተግባር፣ ወይም አጠቃቀም ጋር የሚዛመዱ ድርጊቶች ናቸው።

C. ተገቢ ያልሆኑ ይዘቶች ማለት ህግን ወይም የ MCPS ፖሊሲዎችን እና/ወይም ደንቦችን የሚጥሱ፤ የተማሪዎች ጤና እና/ወይም ደህንነት ላይ አደጋ ሊፈጥሩ የሚችሉ፤ የተማሪን ዕፅ እና አልኮል እና ሲጋራ መጠቀም፣ ወሲብ፣ ህገወጥ ማግለል፣ ወይም ሌላ ህገወጥ ተግባራትን ያበረታታሉ ተብሎ በምክንያታዊነት የሚታሰቡ፤ አፀያፊ፣ ስም አጥፊ፣ ስም የሚያበላሹ፣ የሚሳደቡ፣ ወይም ግለሰቦችን ዝቅ የሚያደርጉ ቋንቋ ወይም ምስሎች የያዙ፤ ወይም በት/ቤት ስራዎች ላይ ከፍተኛ መስተጓጎል ወይም የእቃ አቅርቦት መቋረጥ የሚፈጥሩ ወይም በምክንያታዊነት ይፈጥራሉ ተብለው የሚገመቱ ናቸው፤ ሁሉም በደንብ JFA-RA፦ የተማሪ መብቶችና ሃላፊነቶች ላይ በተቀመጠው መሰረት ነው የሚሆነው።

D. የ *MCPS* ድረ-ገፅ ማለት ለዲስትሪክቱ፣ ለት/ቤቱ እና ለቢሮ ገፆች ለማህበረሰብ ተደራሽ የሆነ ድረ-ገፅ ነው።

E. ድረ-ገፅ አስተዳደር ማለት የት/ቤቱን ወይም የቢሮውን ድረ-ገፅ የመቆጣጠር ዋና ሀላፊነት ያለበት/ባት የት/ቤት ወይም ቢሮ ዳይሬክተር ወይም አስተዳደር ነው። የግንኙነት ዳይሬክተር እና/ወይም የእሱ/የእሷ ተወካይ የ MCPS Web (ድረ-ገፅ) የድረ-ገፅ አስተዳደር ነው።

F. አብነት / *Template* በእያንዳንዱ ገፅ ላይ ወጥነት ያላቸው ክፍሎች ያሉት ሞጁል፣ የተዋቀረ ድረ-ገፅ ነው።

G. ድረ-ገፅ መሪ / *Webmaster* ማለት ለእሱ/እሷ ት/ቤት ወይም ቢሮ ድረ-ገፅ የመፍጠር እና ስራ የማስቀጠል ሀላፊነት የተሰጠው የ MCPS ሰራተኛ አባል ነው። የ MCPS Web ድረ-ገፅ መሪ / Webmaster የሆነው ድረ-ገፅ አገልግሎቶች / Web Services ነው።

H. ድረ-ገፅ አገልግሎቶች / *Web Services*ማለት በግንኙነት ዳይሬክተር መመሪያ ስር፣ የ MCPS Web /ድረ-ገፅን የማስተዳደር ሀላፊነት የተሰጠው ክፍል/ዲፓርትመንት ነው። የግንኙነት ዳይሬክተር ማለት ለ MCPS Web /ድረ-ገፅ የድረ-ገፅ አስተዳዳሪ ነው።

## IV. ቅደም-ተከተሎች/ሂደቶች

A. መስፈርቶች

1. እያንዳንዱ ት/ቤት እና ቢሮ ድረ-ገፅ ወይም ቢያንስ አንድ የድረ-ገፅ ገፅ (Web page) ከአድራሻ መረጃዎች ጋር ሊኖረው ይገባል። ቢሮዎች እና ሌላ የት/ቤት-ያልሆኑ ድረ-ገፆች መሆን ያለባቸው በ MCPS Web /ድረ-ገፅ አብነት/ template ውስጥ ነው። ሁሉም በ MCPS ሰራተኞች በስራ ሀላፊነቶቻቸው ሂደት ውስጥ የተዘጋጁ እና በተማሪዎች በትምህርት ስራዎቻቸው ሂደት ውስጥ የተዘጋጁ ድረ-ገፆች ሊኖሩ የሚገባው በ MCPS-የሚመሩ ስርዓቶች ውስጥ ነው።

2. በ MCPS Web /ድረ-ገፅ ላይ የሚቀመጡ ሁሉም ነገሮች የት/ቤቱን ስርዓት ትምህርታዊ አላማዎች ማገልገል እና ከ MCPS ፖሊሲዎች፣ ደንቦች፣ አስተዳደራዊ አሰራሮች፣ እና የት/ቤት ህጎች ጋር የሚስማሙ መሆን አለባቸው።

3. የድረ-ገፅ አስተዳደሮች፣ ወይም የእነሱ ተወካዮች፣ ለሚከተሉት ስራዎች ሀላፊነት አለባቸው፡-

    a) በ MCPS Web ሰርቨሮች ላይ የት/ቤት ወይም የቢሮ ድህረ-ገፆችን መፍጠር እና ስራ ማስቀጠል፤

    b) በት/ቤት ወይም ቢሮ ድህረ-ገፆች ላይ ለመፍጠር ወይም ስራን ለማስቀጠል ከተመደቡ ግለሰቦች ከድረ-ገፅ አገልግሎቶች የማተም/የመጨመር መብቶችን መጠየቅ እና እነዚህ ሰዎች እነዚህን ተግባራት ለማካሄድ መመደባቸው ሲያበቃ ለድረ-ገፅ አገልግሎቶች ማሳወቅ፤

    c) ማማከር/ማየት ወደ የማውጫ መረጃ መያዣ ዝርዝር በማድረግ የተማሪ መረጃን በግል ለይቶ ለመግለፅ ፈቃድን ማረጋገጥ፤

    d) ይዘቱ ተገቢ፣ ትክክለኛ፣ ጊዜውን የጠበቀ እና ትምህርታዊ አላማዎችን የሚያገለግል እንደሆነ ለማረጋገጥ ድህረ-ገፆች መገምገም፤

    e) ለትምህርታዊ አላማዎች ወይም ለተገቢነት ከእነዚህ መስፈርቶች ጋር መስማማት የማይችሉ ማንኛውንም ይዘት ወይም ሊንኮች ማስወገድ፤ እና

    f) ወደ ድህረ-ገፆቻቸው አዲስ ቴክኖሎጆዎችን ከመፍጠራቸው፣ ንድፍ ከማስተካከላቸው፣ ወይም ከመጨመራቸው በፊት የድረ-ገፅ አገልግሎቶችን ማማከር።

B. ለተገቢ ይዘት መመሪያዎች

1. የድረ-ገፅ ይዘቶች ግልፅ የሆነ ትምህርታዊ አላማ ያላቸው እና ደረጃዎችን በተገቢነት የሚያሟሉ መሆን አለባቸው፣ በ ክፍል 3 (Section III) በተቀመጠው መሰረት። በዚህ ድረ-ገፅ ላይ የሚቀመጡ ሁሉም ነገሮች ከ MCPS ሁሉም ፖሊሲዎች እና ደንቦች ጋር የሚስማሙ መሆን አለባቸው፣ IGT-RA ጨምሮ፡- የተጠቃሚ ሀላፊነቶች ለኮምፒውተር ስርዓቶች እና ኔትዎርክ ደህንነት፣ እና JFA-RA፡- የተማሪ መብቶችና ሃላፊነቶች።

2. በዚህ ድረ-ገፅ ላይ የሚቀመጡ ሁሉም ነገሮች ጊዜውን የጠበቁ/የአሁን እና ትምህርታዊ ደረጃዎችን በፊደላት አፃፃፍ፣ በሰዋሰው፣ በይዘት እና በትክክለኛነት የሚያሟሉ መሆን አለባቸው።

   a. የአሰራር እና በጊዜ-የሚመረኮዙ መረጃዎች፣ ልክ እንደ አድራሻ፣ የት/ቤት ሰአታት፣ የቀን መቁጠሪያ ይዘቶች፣ የሰራተኞች መረጃ ማውጫ፣ እና የት/ቤት መከፈት መረጃዎች አይነት ነገሮች፣ አሁን ላይ በአለው ሁኔታ ተጠብቀው መቀጠል አለባቸው።

   b. ያላለቁ የድር ገፆች እና የድረ-ገፅ ገፆች ነገሮቹ/ይዘቶቹ እስከሚያልቁ ድረስ መታተም የለበትም።

   c. ለማህበረሰብ እይታ ያልታሰቡ ዶሴዎች/ፋይሎች፣ በተለይም የግል እና ሚስጥራዊ ተብሎ ምልክት የተደረገባቸው፣ በድረ-ገፅ ሰርቨሮች ላይ መቀመጥ የለባቸውም።

3. የድረ-ገፅ አገልግሎቶች ለድረ-ገፆችን መስፈርትነት የሚሆኑ መረጃዎችን እና መመሪያዎችን በራሱ ድረ-ገፅ ላይ ያሳትማል። እንደዚህ አይነት መስፈርቶች የሚያካትቱትም መሟላት ያለባቸው ሊንኮችን እና ተገቢ ማሳወቂያ ወይም ይፋዊ ቋንቋን ነው።

4. የማህበረሰብ መወያያ ክፍሎች፣ ፎረሞች፣ የማስታወቂያ ሰሌዳዎች፣ የቡድኖች ውይይት፣ እና ሌላ ተመሳሳይ ቅርፆች ያሏቸው መስተጋብራዊ ግንኙነቶች በ MCPS Web ላይ አይፈቀዱም።

5. በተማሪዎች የሚፈጠሩ እና የሚከናወኑ ድረ-ገፆች የተማሪ ስራ ተብለው መሰየም አለባቸው።

6. የቅጂ መብት

   a. የ MCPS ድረ-ገፅ መሪዎች (webmasters) ከሌሎች ድረ-ገፆች ወይም ግብዓቶች ላይ ይዘቶችን መገልበጥ/መቅዳት እና ይሄንን ይዘት የድረ-ገፅ መሪ፣ ፈጣሪ፣ ባለቤት ወይም የይዘቱ አሳታሚን ፈቃድ ሳያገኙ በ MCPS Web ላይ ማሳተም የለባቸው፣ ይሄም ይዘቱ ለማህበራዊ ጠቀሜታ (public domain) ተብሎ በግልፁ ካልተገለፀ ወይም ባለቤቱ ደግሞ ለመጠቀም ካልፈቀደ ወይም ህጋዊ ፈቃዱን ካልሰጠ ነው።

   b. የት/ቤት እና የቢሮ ድረ-ገፆች ከባለቤቱ የፅሁፍ ፈቃድ ሳያገኙ የባለቤቱን ንግድ ምልክት፣ አገልግሎት ምልክት፣ ወይም አርማ መጠቀም የለባቸውም።

   c. በ MCPS Web ላይ የሚገኙ ድረ-ገፆች የ MCPS ንብረቶች ናቸው፣ ይሄም የተማሪ ስራ ወይም የሌሎችን ግብዓቶች ከፈቃድ ጋር የማያሳዩ ከሆነ ነው። ከ MCPS Web ላይ ይዘትን ደግሞ ለመጠቀም የሚቀርቡ ጥያቄዎች መመራት ያለባቸው ለድረ-ገፅ አስተዳዳሪ ነው።

C. ወደ ውጪ ድረ-ገፆች የሚመሩ ሊንኮች

1. ወደ የ MCPS-ያልሆኑ ድረ-ገፆች የሚመሩ ሊንኮች የ MCPS ትምህርታዊ አላማዎችን የሚደግፉ መሆን ይገባቸዋል፣ ይሄም ከላይ በክፍል ሦስት (Section III) በተቀመጠው መሰረት ነው።

2. ወደ የ MCPS-ያልሆኑ ድረ-ገፆች የሚመሩ ሊንኮች የሚከተለውን ህጋዊ ባለቤትን ማንሻ መያዝ አለባቸው፣ “ይሄ ድረ-ገፅ ከ MCPS ውጪ ወደ ሆኑ አንድ ወይም ከዛ በላይ ድረ-ገፆች የሚያመሩ ሊንኮች ሊኖረው ይችላል። MCPS የእነዚህን ድረ-ገፆች ይዘት ወይም ጠቀሜታ አይቆጣጠርም።” ወደ የ MCPS-ያልሆነ ድረ-ገፅ የሚወስድ በ MCPS Web ላይ የሚገኝ ሊንክ የ MCPS ስፖንሰርነት ለእዚህ ሊንክ የተደረገ አካል አይወክልም።

D. ማስታወቂያ እና የማህበራዊ አገልግሎት ማሳወቂያዎች

1. የ MCPS Web የተከፈለበት ማስታወቂያ ወይም ስፖንሰርነትን ከኮሜርሺያል/ከንግድ አካላቶች አይቀበልም እና የኮሜርሺያል/የንግድ አካላትን አያስተዋውቅም። ለብቻው አንድ የት/ቤት ወይም የቢሮ ድረ-ገፅ የትምህርት አጋር ተብሎ የተለየ እና ለመጠቀም ፈቃድ የሰጠን የንግድ ተቋም ስም፣ አርማ፣ ወይም ምልክት ሊያካትት ይችላል፤ ነገር ግን፣ ድረ-ገፁ ከንግድ አጋሩ ድረ-ገፅ ጋር ሊንክ ሊያደርግ/ማገናኘት የሚችለው

ትምህርታዊ አላማን የሚያገለግል ከሆን ብቻ ነው።

2. በሦስተኛ አካል ያለ ምንም ክፍያ የሚቀርቡ ይዘቶች ወይም የድረ-ገፅ መሳሪያዎች በት/ቤት ወይም በቢሮ ድረ-ገፅ ላይ ጉዳያቸው በተናጠል እየታየ ይፈቀዳሉ። ይዘቱ የ MCPS ትምህርታዊ አላማዎችን ማገልገል፤ ከፈቃድ ጋር ጥቅም ላይ መዋል፤ እና ለአሳታሚ፣ ደራሲ ወይም ባለቤት እውቅና መስጠት አለበት። የሦስተኛ-ወገን ይዘት ወይም መሳሪያዎች/መተግበሪያዎችን የድረ-ገፅ አስተዳደር መፍቀድ አለበት/ባት፤ እና በድረ-ገፁ ላይ ከመካተታቸው በፊት የድረ-ገፅ አገልግሎቶች ማሳወቂያ ሊደርሳቸው ይገባል። ከሦስተኛ-ወገን ይዘት አጠገብ የሚከተለው ህጋዊ ባለቤትን ማንሻ ሊታይ ይገባል— "ይሄ ይዘት ከክፍያ ነፃ የቀረበ ነው እና የ MCPS ፈቃድ ወይም ስፖንሰር ማድረግን አያመላክትም።"

E. የተማሪ መረጃ ሚስጥራዊነት

1. ድረ-ገፅ ከሁሉም ተግባራዊ ከሚሆኑ የሚስጥራዊነት ህጎች እና ደንቦች ጋር የሚስማማ መሆን አለበት።

2. የማውጫ መረጃ መያዣ ዝርዝርበድረ-ገፅ ላይ በግል የሚለይ መረጃን ለመጠቀም ተቀዳሚ የፈቃድ ምንጭ/ግብዓት መሆን አለበት። መቼም ቢሆን የተማሪ የቤት አድራሻ፣ ስልክ ቁጥር፣ ኢሜል አድራሻ፣ የትውልድ ቀን፣ የማህበራዊ ደህንነት ቁጥር፣ ወይም በስቴት ወይም ፌደራል ህግ ሚስጥራዊ የተደረገ መረጃ በድረ-ገፁ ላይ መታየት የለበትም። ድረ-ገፁ የተማሪዎችን በአንድ ወቅት ላይ አካላዊ መገኛ ቦታ የሚሰጥ ማንኛውንም መረጃ ማካተት የለበትም።

F. የድረ-ገፅ አገልግሎቶች / Web Services ሀላፊነቶች

1. የድረ-ገፅ አገልግሎቶች፣ ለግንኙነት ዳይሬክተር ሪፖርት የሚያደርጉ ሲሆን፣ ይሄን ደንብ የመተግበር፣ የ MCPS Web ስራ የማስቀጠል እና የማዳበር፣ ለት/ቤት እና ቢሮ ድረ-ገፆች ፈቃድን የማስተዳደር፣ እና ሁሉንም የድረ-ገፅ ተግባራት ከትምህርት ቦርድ ፖሊሲዎች፣ ተግባራዊ ከሚሆኑ ህጎች እና ደንቦች፣ እና ከዚህ ደንብ ጋር ተስማሚ መሆኑን መቆጣጠር አለባቸው።

2. በድረ-ገፆች ላይ ይዘቶችን ለማዘጋጀት እና ለማሳተም MCPS የቴክኒካዊ መስፈርቶችን፣ ድጋፍ እና ስልጠና ማቅረብ አለበት።

3. የድረ-ገፅ አገልግሎቶች ዳይሬክተር እና/ወይም የግንኙነት ዳይሬክተር በዲስትሪክት፣ በት/ቤት ወይም በቢሮ ድረ-ገፆች ላይ ችግር ያለበት ይዘትን ለይቶ ካገኘ/ች፣ ከዚህ

ደንብ ጋር ተስማሚ እንዲሆን ለድረ-ገፅ አስተዳደር ማሳወቅ እና ችግር ያለበትን ይዘት ለማስተከከል ወይም ለማስወገድ መጠየቅ አለበት/ባት።

4. ከዚህ ድረ-ገፅ እና ከእነዚህ ደንቦች የታሰበላቸው አላማዎች ጋር ተስማሚ እንዲሆን ማንኛውንም በድረ-ገፁ ላይ የሚገኝ ይዘት MCPS ትክክል ነው በሚለው መልኩ አርትዖት/ማስተካከያ የማድረግ፣ የመሰረዝ፣ ወይም የማሻሻል መብት አለው።

5. የዚህ ደንብ ጥሰቶች፣ ደንብ IGT-RA፦ ለኮምፒውተር ስርዓቶች እና ለኔትወርክ ደህንነት የተጠቃሚ ሀላፊነቶች፣ ወይም ደንብ JFA-RA፦ የተማሪ መብቶች እና ሀላፊነቶች፣ የማሳተም ፈቃዶችን በማጣት ወይም የዲሲፕሊን እርምጃ ሊያስከትል ይችላል፣ በ IGT-RA፣ ክፍል 4 (Section IV.F) ውስጥ በተቀመጠው መሰረት።

ስለ ደንቡ ታሪክ፦ አዲስ ደንብ፣ ሴፕቴምበር 11፣ 2006።